**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 022284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה ארבעה פרקים.

ענה על שאלה אחת מכל פרק.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שני | — (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שלישי | — (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק רביעי | — (25x1) | — | 25 נקודות |
| | סה"כ | — | 100 נקודות |

**שים לב**: תלמידים **שאושר להם מבחן מותאם** יענו על שלוש שאלות: שאלה אחת מפרק ראשון **או** מפרק שני, שאלה אחת מפרק שלישי ושאלה אחת מפרק רביעי.

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

כתוב במחברת הבחינה בלבד. רשוֹם "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.

כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ወቅት: የ2019 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 022284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

ጰ. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና አራት ምዕራፎችን ይዟል።

ከእያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ ጥያቄ መልስ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | — (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ አራት | — (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| | በአጠቃላይ | — | 100 ነጥብ |

**ልብ በል፦ ተስማሚ ፈተና** (מבחן מותאם) **የተፈቀደላቸው** ተማሪዎች ሦስት ጥያቄዎችን ይመልሱ፦ ከምዕራፍ አንድ **ወይም** ከምዕራፍ ሁለት አንድ ጥያቄ፣ ከምዕራፍ ሦስት አንድ ጥያቄ እና ከምዕራፍ አራት አንድ ጥያቄ።

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ ጻፍ። ለማስቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት።

ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ማስቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ቅሉ ለሴትም ለወንድም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (25 ነጥብ)

## የመጀመሪያው ወቅት፦ ብሔርተኝነት በእስራኤልና በሕዝቦች ዘንድ - ከጅማሬው እስከ 1920

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**1. ብሔርተኝነት**

ለ. በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከአውሮፓ የብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ዓላማዎች ውስጥ ሁለቱን አቅርብ። (10 ነጥብ)

ለ. የአብርሆ እንቅስቃሴ (תנועת ההשכלה) በአውሮፓ ውስጥ በብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች ዕድገት ላይ ያደረገውን ተጽዕኖ አብራራ እና በዚህ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ያደረሰ አንድ ታሪካዊ ክስተት አቅርብ። (15 ነጥብ)

**2. ሔርጼል እና የጽዮናዊነት እንቅስቃሴ**

ለ. በባዝል ዕቅድ (תוכנית בזל) መሠረት የጽዮናውያንን እንቅስቃሴ ዓላማ አቅርብ እና በባዝል ዕቅድ እና በኡጋንዳ ዕቅድ (תוכנית אוגנדה) መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ። (13 ነጥብ)

ለ. "ቻርተር" ("צ'רטר") ምንድን ነው? ቻርተር ("צ'רטר") በእስራኤል አገር ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ ሔርጼል ያደረጋቸውን ሁለት ድርጊቶች አሳይ/ግለጽ። (12 ነጥብ)

**3. ከ1882–1914 ባሉት ዓመታት ወደ እስራኤል አገር መግባት (ዓልያ ማድረግ)**

ለ. ከ1882-1914 ባሉት ዓመታት ውስጥ ለይሁዳውያን ወደ እስራኤል ሀገር መግባት/መምጣት መንስኤ የሆኑትን ሦስት ነገሮች አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የነበሩት አዲስ ገቢዎች በሠፈራ፣ ባሕል እና ደህንነት ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ነበር።
አዲስ ገቢዎቹ ከእነዚህ ዘርፎች ውስጥ በአንዱ ያደረጉትን እንቅስቃሴ አቅርብ እና ይህ ለጽዮናዊነት ያለውን አስፈላጊነት አብራራ። (13 ነጥብ)

ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ ሁለት (25 ነጥብ)

### ሁለተኛው ወቅት፦ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል (ከ1920-1939)፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች ወቅት የይሁዳውያን ሠፈራ በእስራኤል አገር

ከ4-6 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> መልስ።

**4. <u>"የዊልሰን 14 ነጥቦች" እና ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የአመራር ለውጦች</u>**

**አ.** ከ"ዊልሰን 14 ነጥቦች" ሰነድ ውስጥ <u>ሦስት</u> ንውሳን አንቀጾችን አቅርብ። (12 ነጥብ)

**ኔ.** በአንደኛው የዓለም ጦርነት የተሸነፉት ኃያላን ሀገራት እነማን ነበሩ? ከጦርነቱ በኋላ የመጡ <u>ሁለት</u> ለውጦችን አቅርብ፦ አንድ <u>በአውሮፓ</u> የፖለቲካ ካርታ ላይ የመጣ ለውጥ እና አንድ <u>በመካከለኛው ምሥራቅ</u> የፖለቲካ ካርታ ላይ የመጣ ለውጥ። (13 ነጥብ)

**5. <u>በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የይሁዳዊያን ሠፈራ - በእስራኤል ሀገር</u>**

**አ.** በዚህ ወቅት በእስራኤል አገር ውስጥ የተቋቋሙትን <u>ሁለት</u> አዳዲስ የአሠፋፈር መልክ መለያዎችን አቅርብ። (13 ነጥብ)

**ኔ.** በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አሥራ ዘጠኝ ሰላሳዎቹ ዓመታት ውስጥ የይሁዳዊያን ሠፈራዎች <u>በባሕል</u> ዘርፍ እና <u>በኢኮኖሚ</u> ዘርፍ ላይ የነበሯቸውን ስኬቶች አቅርብ። (12 ነጥብ)

**6. <u>በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሰላሳዎቹ ዓመታት ይሁዳዊያን፣ አረቦች እና ብሪታንያዊያን በእስራኤል ሀገር</u>**

**አ.** በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሰላሳዎቹ ዓመታት ላይ በእስራኤል አገር ይሁዳዊያን እና አረቦች መካከል የነበረው ውጥረት እንዲባባስ መንስኤ የሆኑትን <u>ሁለት</u> ምክንያቶች አብራራ እና የዚህን ውጥረት <u>አንድ</u> መግለጫ አቅርብ። (13 ነጥብ)

**ኔ.** የሦስተኛውን "ነጭ መጽሐፍ" አንቀጾች አቅርብ እና በእስራኤል አገር ያለው የይሁዳዊያን ሠፈራ ለምን ይህን መጽሐፍ እንደተቃወመ አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ ሦስት (25 ነጥብ)

### ሦስተኛው ወቅት፦ አምባገነኑ መንግሥት (המשטר הטוטליטרי)፣ ናዚነት፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የይሁዳውያን መጨፍጨፍ (השואה)

ከ7-10 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> መልስ።

**7.** **<u>ጀርመን - ከዲሞክራሲ ወደ የናዚ ግዛት (משטר הנאצי)</u>**

**ሀ.** ከሚከተሉት እርምጃዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> አቅርብ፦ የሪቻክስታግ ነበልባል (שְרֵפַת הרייכסטג) <u>ወይም</u> የረጃጅሞቹ ቢላዋዎች ምሽት (ליל הסכינים הארוכות)፣ እና ይህ ርምጃ ጀርመኖች ከዲሞክራሲያዊነት ወደ ናዚ አገዛዝ እንዲሸጋገሩ እንዴት እንደረዳቸው አብራራ። (12 ነጥብ)

**ለ.** በናዚ ርዕዮተ-ዓለም (אידאולוגיה) የዘረኝነትን (אנטישמיות) መርሆ አብራራ እና <u>እስከ</u> ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍንዳታ ድረስ የናዚ አገዛዝ ይህን መርሆ ለማራመድ በጀርመን ውስጥ ያደረጋቸውን <u>ሁለት</u> እርምጃዎች አቅርብ። (13 ነጥብ)

**8.** **<u>ማጎሪያዎቹ (הגטאות)</u>**

**ሀ.** ናዚዎች በማጎሪያው ዮዴራንቶች ላይ የጣሉባቸውን <u>ሁለት</u> የሥራ ድርሻዎች አቅርብ እና በማጎሪያዎቹ ላይ ተጨማሪ አንድ መቆጣጠሪያ መንገድ (ከዮደራንቱ ውጭ) አቅርብ። (12 ነጥብ)

**ለ.** በማጎሪያዎቹ የነበሩ ይሁዳዊያንን <u>ሦስት</u> ችግሮች አቅርብ እና በማጎሪያው የነበራቸውን የሕይወት ችግር ለመቋቋም የ"ቅዱስ ሕይወት" ("קידוש החיים") ራዕይ እንዴት እንደረዳቸው አቅርብ። (13 ነጥብ)

**9.** "**<u>የመጨረሻው መፍትሔ" ("הפתרון הסופי")</u>**

**ሀ.** ጀርመን ወደ ሶቭየት ኅብረት ሰብራ በገባችበት ጊዜ በይሁዳዊያን ላይ ያደረገችው የመመሪያ ለውጥ ምን ነበር? ለእነዚህ ለውጦች ምክንያት ከሆኑት <u>ሁለቱን</u> አብራራ። (12 ነጥብ)

**ለ.** <u>ይሁዳዊያን ያልሆኑ</u> ነዋሪዎች ከናዚዎች ጋር ለመተባበር ተጽዕኖ ያደረጉባቸውን <u>ሁለት</u> ምክንያቶች እና "በመጨረሻው መፍትሔ" ጊዜ <u>ይሁዳዊያን ያልሆኑ</u> ነዋሪዎች ይሁዳዊያንን ለመርዳት ተጽዕኖ ያደረጉባቸውን <u>ሁለት</u> ነገሮች አብራራ። (13 ነጥብ)

**10.** **<u>የማጎሪያዎቹ ዓመጻዎች (המרד בגטאות)</u>**

**ሀ.** ከ1942 ጀምሮ በጌቶ (በማጎሪያው) ለምንድን ነው ዓመፅ የጀመረው? የዓማፂያኑን <u>ሁለት</u> ዓላማዎች አብራራ። (12 ነጥብ)

**ለ.** የጌቶው (የማጎሪያው) አመፅ ድርጅትን <u>ሁለት</u> ችግሮች አቅርብ። የቫርሻ ጌቶን አመፅ ልዩ የሚያደርገውን (דוחיי) አብራራ። (13 ነጥብ)

ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ አራት (25 ነጥብ)

## አራተኛው ወቅት፦ እስራኤል ሀገርን በመካከለኛው ምሥራቅ መገንባት

ከ11-14 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**11. የእስራኤል አገር ጥያቄ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት**

**ሀ.** ብሪታንያ የእስራኤል አገርን ጥያቄ ወደ ተባበሩት መንግሥታት እንድታስተላልፍ ተጽዕኖ ያደረጉባትን ሁለት ምክንያቶች አብራራ፦ በእስራኤል አገር ካሉ የይሁዳዊያን ሠፈራዎች ጋር የተያያዘ አንድ ምክንያት እና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከነበረው የብሪታንያ ሁኔታ ጋር የተያያዘ አንድ ምክንያት። (10 ነጥብ)

**ለ.** ኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተወሰነውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ አቅርብ።
ከውሳኔው የትኛው ንዑስ አንቀጽ ይሁዳዊያንን እንዳስደሰታቸው እና የትኛው ንዑስ እንዳሳሰባቸው አብራራ።
(15 ነጥብ)

**12. በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሃምሳዎቹ እና ስድሳዎቹ ዓመታት ወደ እስራኤል ሀገር መግባትና መስተንግዶ**

**ሀ.** በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳዎቹ እና ስድሳዎቹ ዓመታት ላይ ወደ እስራኤል አገር ለመግባት (ለዓልያ) ምክንያት ከሆኑት ሁለቱን አብራራ፦ ከእስላም አገራት ወደ እስራኤል ለመግባት አንድ ምክንያት እና ከአውሮፓ ወደ እስራኤል ለመግባት አንድ ምክንያት። (10 ነጥብ)

**ለ.** የቫዲ ሳሊብ (ואדי סאליב) ክስተቶችን ግለጽ እና ወደ እነዚህ ክስተቶች የመሩ የአዲስ ገቢዎችን ሁለት ችግሮች አብራራ። (15 ነጥብ)

**13. የእስራኤል ማኅበረሰብ በ"ሾአ" መታሰቢያ ላይ ያመጣው የአመለካከት ለውጥ**

**ሀ.** የአይኽማን ፍርድ ምን ነበር? የእስራኤል ማኅበረሰብ ከአይኽማን ፍርድ በኋላ "גבורה" በሚለው መግለጫ ላይ ያመጣውን የአመለካከት ለውጥ አብራራ። (15 ነጥብ)

**ለ.** የእስራኤል ማኅበረሰብ ከ"ሾአ" በተረፉት ላይ ባለው አመለካከት ላይ የእስራኤል ጦርነቶች ያመጡትን ተጽዕኖ አብራራ። (10 ነጥብ)

**14. የስድስቱ ቀን ጦርነት/ የአስተሰርዮ ጦርነት (מלחמת ששת הימים / מלחמת יום הכיפורים)**

ከሁለቱ ጦርነቶች አንዱን ምረጥ፦ የስድስቱ ቀን ጦርነት (1967) ወይም የአስተሰርዮ ጦርነት (1973)።

**ሀ.** በመረጥከው ጦርነት የተዋጉት እነማን ናቸው?
ጦርነቱ ሲፈነዳ የትኛው ጐን ነው ድንገተኛ የሆነበት? ለምን ድንገተኛ እንደሆነበት አብራራ።
(12 ነጥብ)

**ለ.** የመረጥከውን ጦርነት ፈጣን ውጤቶች አሳይ እና በጦርነቱ ምክንያት በተነቃቃው የእስራኤል ማኅበረሰብ ስሜት ላይ እነዚህ ውጤቶች እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረጉ አብራራ። (13 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך